# "ኢትዮጵያ የከሸፈች ሀገር እየሆነች ነው" ሻለቃ ዳዊትወልደጊዮርጊስ

## BBC AMHARIC

## https://www.bbc.com/amharic/news-47879359

በደርግ ስርዓት ከፍተኛ ባለስልጣን የነበሩትና በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ ጉዳዮች ተመራማሪ የሆኑት ሻለቃ ዳዊትወልደጊዮርጊስ "ኢትዮጵያ በቀውስ አፋፍ ላይ ናት" የሚል ጽሑፍ ፅፈው በተለያዩ ድረ ገፆችና በማህበራዊ ሚዲያሲዘዋወር ነበር። ቢቢሲ ያነጋገራቸው ሻለቃ ዳዊት የጽሑፋቸው አላማ ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ ማስረዳት እንደሆነይናገራሉ። ኢትዮጵያ እየወደቀች ነውም ብለዋል።

**ሻለቃ ዳዊት፡** የጽሁፌ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ ማስረዳት ነው። በሃገሪቱ የሚከናወኑ ብዙ ነገሮች ስላሉ ህዝቡተወጥሮ ያለው በዕለት ተዕለት ጉዳዮች ላይ ነው። እነዚህ ሁሉ ግን ተደምረው በጠቅላላ የሃገሪቱ ስእል ምን ይመስላልየሚለውን ለማሳወቅ ነው የፈለግኩት። እናም በደህንነት ረገድ፣ በኢኮኖሚና በአጠቃላይ በአመራር ደረጃ ያለውንስንመረምረው ጠቅላላ ኢትዮጵያ የከሸፈች ሃገር ( failed state) ወይም ከቁጥጥር ውጪ የሆነች አፍሪካዊ ሃገር እየሆነችነው። ቁጥሮቹን በሙሉ ጽሁፌ ላይ አስቀምጫለው።

እኔ ያደረግኩት በሜዳ ላይ የሚታዩትን ሃቆች አውጥቶና ስእሉ ሲደመር የኢትዮጵያ አቅጣጫ ምን ይመስላል? የሚለውንለመመለስ ነው የሞከርኩት። አቅጣጫው አደገኛ አቅጣጫ ነው። አመራሩ አስፈላጊና ከባድ ውሳኔ ካልወሰነ በስተቀር አዘቅትውስጥ ገብታ ምናልባትም የእርስ በርስ ጦርነት ሊያመጣ የሚችል ሁኔታ ይፈጠራል። ይህንን ለማስቀረት መደረግስለላባቸው ነገሮችም ጠቁሜያለው።

ምናልባት መደረግ ያለባቸው ነገሮች አስቸጋሪና ከባድ ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን በከባድና አስቸጋሪ ጊዜ ከባድና አስቸጋሪውሳኔ መወሰን ያስፈልጋል። በእንደዚህ አይነት ጊዜ ያሉ አመራሮችም መጥፎ ሁኔታ ላይ እንዳለን ሲያውቁ መደረግ ያለበትውሳኔ መራራ ሆኖ፤ ነገር ግን በረጅም ጊዜ ኢትዮጵያን የሚያድን ይሆናል እንጂ ስለፍቅር በመናገርና ህዝቡን በማባበል፤ ተስፋ በመስጠት ያጋጠመንን ችግር መፍታት አይቻልም ለማለት ነው።

## ሃገሪቱ አዲሱ አስተዳደር ከመምጣቱ በፊት ከነበረው የባሰ ሁኔታ ውስጥ ናትማለት ይቻላል?

**ሻለቃ ዳዊት፡** አዎ፤ በጣም እንጂ፤ በትክክል። በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያን በመፈናቀል ደረጃ የወሰድን እንደሆነ፣ ድሮምጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ከመምጣታቸው በፊትም ነበረ። አሁን ግን በጠቅላላው በጣም እየባሰ መጥቶ በአፍሪካውስጥ ትልቁ በሚባል ደረጃ ብዙ ሰው የተፈናቀለባት ሃገር ኢትዮጵያ ናት። እስከ አራት ሚሊየን ህዝብ ተፈናቅሏል።

በጠቅላላው ደግሞ የሃገሪቱ የደህንነት ሁኔታ ስንመለከት አንድ ሃገር ውስጥ በነጻነት መንቀሳቀስ የማይቻልበት ሁኔታ ነውያለው። እንደዚህ አይነት ነገሮች ደግሞ የሚፈጠሩት እንደ ደቡብ ሱዳን፣ ሶማሊያና ማዕከላዊ አፍሪካ ባሉ የከሸፉ ሃገራትነው።

በግለሰብ ደረጃ ስንመለከተው ደግሞ እያንዳንዱ ሰው በስጋት ነው የሚኖረው። ሲወጣም ሆነ ሲገባ በስጋት ውስጥ ሆኖነው። የኢኮኖሚውን ዘርፍ ያየነው እንደሆነ ሌላው ቀርቶ መድሃኒትና ነዳጅ ለመግዛት የሚያስችል የውጭ ምንዛሪ ብቻእንጂ ከዚያ ውጪ ባንክ ውስጥ ምንም መጠባበቂያ እንደሌለ ብሔራዊ ባንክ ተናግሯል።

ከዚህ በተጨማሪ አሁን እያስተዋልነው ያለነው መሰዳደብና መዘላለፍ በህዝብ መሃል ያለውን ተቃርኖ እያባባሰው ሄዷል። ይሄ ሁሉ የአመራርና የፖሊሲ ጉዳይ ነው። አመራርና ፖሊሲ እስካልተቀየረ ድረስ ይሄ ሊለወጥ አይችልም። እንደዚህአይነት ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው። ሃገሪቱ በእኔ እድሜ በኃይለስላሴም፣ በደርግም ሆነ በኢህአዴግ እንደዚህ አይነት አሳሳቢሁኔታ ላ ይ ደርሳ አታውቅም።

## ይሄ ችግር ከዚህ በፊት ሲጠራቀም የመጣ እንደመሆኑ አሁን እንዴት በጣምአሳሳቢ ሊሆን ይችላል?

**ሻለቃ ዳዊት፡** የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ወደ ስልጣን ከመምጣት ጋር ተያይዞ የህዝቡ ችግር የነበረውን አስወግዶአዲ ስ ምዕራፍ ለኢትዮጵያ ይከፍታል የሚል እምነት ነበር። ስለዚህ ቃል በተገባው መሰረት የተባለው ነገር ስላልተደረገችግሩ ቀስ እያለ መፈንዳት ጀምሯል። ይህ ማለት ግን ችግሩ የአንድ ሰው ጥፋት ነው፤ ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር አብይአህመድ ችግር ነ ው ለማለት ሳይሆን እሳቸው ወደ ስእሉ ሲገቡ ችግሩን አስወገደው ሃገሪቱን ወደ አዲስ ምዕራፍ ያሸጋግራሉየሚል እምነት ነበረ ። ቃል የተገባው ነገር አልተፈጸመም። ባለመደረጉ ደግሞ እዚህ ደረጃ ላይ ደርሰናል።

## እርሶ የጠቀሷቸው ነገሮች በሽግግር ወቅት የሚያጋጥሙ ናቸው የሚሉ ሰዎችአሉ

**ሻለቃ ዳዊት፡** አልተሸጋገርንም፤ ለውጥም የለም። ለውጥ ማለት የስርአት ለውጥ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብም የጠየቀውየስርአት ለውጥ ነው። እዚህ ችግር ውስጥም የከተተን የነበረው ስርአት ነው። አብዛኞዎቹ ነገሮች እንዳሉ ናቸው። እስከ ዛሬድረስ ተቀየ ሩ የሚባሉት ነገሮች በስርአት አቅጣጫ ሳይሆን ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ በግል በወሰዷቸውእርምጃዎች ነው። ነገር ግን ይሄ ለለውጡ ሁኔታውን ለማመቻቸት ነው እንጂ በራሱ እንደ ለውጥ ልንመለከተውየምንችለው ነገር አይደለም።

እስካሁን ለተፈጠሩት ችግሮች በሙሉ ኢህአዴግን ተጠያቂ ማድረግና ኢትዮጵያ በአዲስ ህገመንግስት አዲስ ምርጫ ውስጥእን ድትገባ ማድረግ ነው ትክክለኛው ለውጥ። ጠቅላዩ በስልጣን ለአንድ ዓመት ቆይተዋል፤ በአንድ ዓመት ውስጥም ምንምነገር አ ልታየም።

ይህ የሆነው ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ፍኖተ ካርታ ስለሌላቸው ወዴት አቅጣጫ እንደሚኬድ አያውቁትም። ሕገ-መንግሥቱ እንዴት እንደሚሻሻልና ወደ አዲስ ምርጫ እንዴት መሄድ እንደምንችል ትክክለኛ አቅጣጫ ማስቀመጥ የሚችልፍ ኖተ ካርታ ያስፈልገናል።

**መሰረታዊ የህግ ለውጦች ካስፈለጉ ሙሉ የህዝብ ውክልና ያለው መንግስት ነው ሕገ-መንግሥቱን መቀየር ያለበት?**

**ሻለቃ ዳዊት፡** በአሰራሩ መሰረት ለውጥ የሚመጣው ወይም ሕገ-መንግሥትን የሚፈጥረው መንግሥት ሳይሆን ሕገ-መንግሥቱ ነው ስልጣን ያለው መንግስት መፍጠር የሚችለው። አሁን ለውጡ ይካሄድ ሲባል ባለው ሕገ-መንግሥትናባለው መንግሥት ለውጥ ሊካሄድ አይችልም። ለውጥ ሊመጣ የሚችለው አዲስ ሕገ-መንግሥትና አዲስ መሰረታዊ ሃሳቦችተፈጥረው ሲታዩ ነው።

ያለው መንግሥት እንዳለ ሆኖ ለውጥ ሊመጣ አይችልም። እነዚህን ሁሉ ችግሮች የፈጠረው ጠቅላዩ የሚመሩት ኢህአዴግነው ። ምናልባት እሳቸው በቀጥታ ላይመለከታቸው ይችላል፤ ነገር ግን ፓርቲው ለብዙ ነገር ተጠያቂ ነው። ስለዚህ ሕገ-መንግሥቱ ፈርሶና አዲስ መንግሥት መጥቶ ነው ለውጥ ልንመለከት የምንችለው።

## ሁሉንም ሰው የሚያስማማ ነገር ማምጣት ይቻላል? ሕገ-መንግሥቱን ማንሳቱወደሌላ ቀውስ አይመራም?

**ሻለቃ ዳዊት፡** ቀውስማ አሁንም ተፈጥሯል። ከዚህ የባሰ ቀውስ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈጠር አይችልም። ስለዚህ ዋናው ነገርለዘለቄታው ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር እንድትኖር ከባድ ውሳኔ መስጠት አለበት። ዋናው ችግራችን የምንከተለው በዓለምውስጥ የሌለ የብሄር ፌደራሊዝም ነው። ይህ ስርአት በዓለም የለም፤ በአፍሪካም የለም። ትንሽ ተቀራራቢ አሰራር ያለውኮሞሮስና ናይጀሪያ ውስጥ ነው። እሱም ቢሆን በዋነኛነት በዘር ላይ የተመሰረተ አይደለም።

የብሄር ፌደራሊዝሙም ቢሆን ህዝቡን አማክሮ አወያይቶ አልነበረም ተግባራዊ የተደረገው። ሕገ-መንግሥቱን ሲያረቅቁትትልቅ ስህተት ተሰርቷል። የቀድሞው ፕሬዝዳንት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ራሳቸው ተሳስተናል፤ ህዝቡን አላማከርነውም ነበርብለዋል። እኔ እያልኩ ያለሁት ህዝቡ በደንብ ይመከርበትና አዲስ ሕገ-መንግሥት ይፈጠር ነው።

ይህንን የብሄር ፌደራሊዝም ይዘን ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም ይመጣል ብሎ ማሰብ አይቻልም። ሰላም አለመገኘት ብቻሳይሆን እልቂት ይፈጠራል፤ ምንም ጥርጥር የለውም።

## አሁን እየጠቀሱት ላለው ችግር መፍትሄው ምንድነው ይላሉ?

**ሻለቃ ዳዊት፡** መፍትሄው በቀላሉ የሚገኝ ነገር አይደለም። የደፋር እርምጃ ያስፈልጋል። በእንደዚህ አይነት የችግር ጊዜያትየሚመጡ ብዙ መሪዎች ጠንካራ ውሳኔ መወሰን መቻል አለባቸው። ቀላል ነገር ቢሆን ኖሮ ማንም ሰው ያደርገው ነበረ።

በጽሑፌ ላይ ለመጠጥቀስ እንደሞከርኩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ካልቻሉ፤ አልቻልኩም ብለው ከስልጣን ይልቀቁና አማራወይንም ኦሮሞ ያልሆነ ሰው ስልጣኑን ይረከብ። ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት ያለው ችግር በአማራና በኦሮሞ መካከል ያለውፉክክርና በሁሉም ዘርፍ ያለው ሽሚያ ነው።

ወደ ሽግግር ሊያመጣን የሚችል መሪ ያስፈልገናል። ሁለተኛ ያለን አማራጭ ደግሞ፤ እሺ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይቆዩ የሚባልከሆነ ሕገ-መንግሥቱ ፈርሶና የኢህአዴግ ፓርላማ ተበትኖ እሳቸው በአዋጅ አሸጋጋሪ ሆነው የሃገሪቱን አጀንዳ ይዘው መሄድአለባቸው።

አሁን ችግር የሆነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢህአዴግ ሊቀመንበርና የኦሮሞ ዴሞክራቲክ ፓርቲ ሊቀመንበርም ናቸው። ሁለቱአብሮ ሊሄድ አይችልም። መምረጥ መቻል አለባቸው። ወይ የኢትዮጵያ መሪ አልያም የኦሮሞ መሪ መሆን አለባቸው። የሁለቱም መሪ ሊሆኑ አይችሉም።

የኦሮሞን ህዝብ ጥቅም አስጠብቃለሁ እያሉ የኢትዮጵያውያንን ጥቅምም አስጠብቃለሁ ማለት አይችሉም። በሌሎች ሃገራትእኮ ሙሉ ሃገሪቱን የሚወክል ፓርቲ ነው ያለው። ስለዚህ ጠቅላይ ሚኒስትራችን ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ይዘው፤ ከዘረኛፖለቲካ ወጥተው መምራትና ማሸጋገር ይችላሉ። ግን ይሄንን ለማድረግ ሕገ-መንግሥቱ መፍረስ አለበት።

የዘር ድርጅቶች የሲቪክ ድርጅቶች ሆነው የህዝቦቻቸውን መብቶች የሚያስጠብቁበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። የፖለቲካድርጅቶች መሆን አይችሉም የሚል ህግ መውጣት አለበት።

**ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ እየሰሩ እንደሆነ አያምኑም?**

**ሻለቃ ዳዊት፡** ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኦሮሞ ዴሞክራቲክ ፓርቲ መሪ ናቸው። ስለዚህ ፓርቲያቸው የሚፈልገውን ነገርመፈጸም አለባቸው። በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያውያንን አጀንዳ መያዝ አለባቸው፤ ይሄ ደግሞ ይጋጫል። አሁንየምናያቸው ችግሮች ሁሉ የተፈጠሩት በሁለቱ ሃላፊነቶች መጋጨት ምክንያት ነው።

ይህንን ጠንካራ ውሳኔ ለመወሰን ብዙ ሥራና መነጋገር ይጠይቃል። የኢትዮጵያን አጀንዳ ይዞ በየሃገሩና በየክፍለሃገሩመናገርና ሰዉን ማሳመን መቻል አለባቸው። መጀመሪያ ላይ እኮ ህዝቡ ከፈጣሪ በታች አድርጎ የተቀበላቸው ኢትዮጵያዊአጀንዳ ይዘው

በመምጣቻው ነበር። አሁን ግን እሳቸው የኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን የኦሮሞ ህዝብንና የኦዴፓን ጥያቄይዘው ነው የመጡት
።